የቤተሰብ የመረጃ ሰነድ

# ጤናማ በመሆን እና ባለመሆን መካከል መሆንን የሚያሳይ ውጤት፦ የወድያው ደም ምርመራ ውጤት ማሳወቂያ

የሚኔሶታ አዲስ የተወለዱ ህጻናት ምርመራ ፕሮግራም

**Elevated CK-MM, Family Fact Sheet—Amharic**

# ከፍ ያለ CK-MM

## አዲስ በተወለዱ ህጻናት ምርመራ የተገኘው ምን ነበር?

ከወሊድ በኋላ የሚሰበሰበው የአዲስ ተወላጅ ህጻናት ምርመራ ልጅዎ ክሪያቲን - ኪናስ (CK-MM) ተብለው የሚጠሩት ከፍተኛ የጡንቻ ኢንዛይም ደረጃዎች እንዳሉበት አሳይቷል።

## ይህ ምን ማለት ነው?

ከወሊድ በኋላ በአዲስ የተወለዱ ህጻናት ላይ በሚካሄድ ምርመራ ናሙና ከፍተኛ CK-MM መገኘት የተለመደና በአብዛኛው በመደበኛ የወሊድ ሂደት ወቅት የሚያጋጥም ነው። ይህ በተለይም ልጁ በአስቸጋሪ ወሊድ፣ ከጉዳት ጋር ከተወለደ እና ወደ NICU ከገባ፣ ወይም የአዲስ ተወላጅ ህጻን ምርመራው ቀደም ብሎ ከተሰበሰበ ያጋጥማል። በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት CK-MM በምርመራው ወቅት የተለመደ ነው።

አልፎ አልፎ ይህ የምርመራ ውጤት እንደ የዱቼን የጡንቻ ዲያስትሮፊ (DMD) ወይም የቢከር የጡንቻ ዲያስትሮፊ (BMD) በመሳሰሉ የጡንቻ እክሎች ምክንያት ይፈጠራል። ግለሰቦች አንዱ እነዚህ የጡንቻ እክሎች ካሉባቸው CK-MM በጊዜ ሂደት ከፍ እንደሚል ይጠበቃል።

## ቀጥሎ ምን ይሆናል?

በልጅዎ ላይ DMD/BMD የመኖር እድሉ አነስተኛ ቢሆንም እንኳ በእርግጠኝነት ለማወቅ ተጨማሪ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

የልጅዎ ዶክተር ልጅዎ ቢያንስ ሁለት ሳምንት እድሜ ሲሞላው ድጋሚ የአዲስ ተወላጅ ህጻን ምርመራ ውጤት ይሰበስባል። አብዛኞቹ የድጋሚ ምርመራ ውጤቶች መደበኛ ስለሚሆኑ ምንም ሌላ ምርመራ ማድረግ አያስፈልግም።

CK-MM ከፍተኛ ሆኖ ከቀጠለ የልጅዎ ዶክተር በጡንቻ ሁኔታዎች ላይ የበለጠ ልምድ ባላቸው ስፔሻሊስቶች ተጨማሪ ምርመራ የሚደረግበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

## ለጨቅላ ህጻናት የ DMD/BMD ምርመራ የሚደረግላቸው ለምንድን ነው?

DMD እና ተያያዥ BMD ተብሎ የሚጠራው ሁኔታ በጨቅላ ህጻንነት ወቅት የሚታዩ የጡንቻ እክሎች ናቸው። እነዚህ ከፍተኛ የጡንቻ መድከምና በጊዜ ሂደት የጡንቻ አለመስራት ያስከትላሉ። እነዚህ እክሎች በዋናነት የሚያጠቁት ወንዶችን ሲሆን ሴቶች በአብዛኛው ምንም ምልክቶች አይታዩባቸውም ወይም መጠነኛ ምልክቶች ይታዩባቸዋል።

DMD/BMD ሊታከም የማይችል ቢሆንም በቅድሚያ የሚደረጉ ጣልቃገብነቶች በሽታውን ለማዘግየትና የአኗኗር ጥራትን ለማሻሻል ሊያግዙ ይችላሉ።

## መርጃዎች

**የዘረመል መነሻ ማጣቀሻ፦**
http://ghr.nlm.nih.gov

Save Babies Through Screening Foundation:
www.savebabies.org

**የልጅ የመጀመሪያ ምርመራ፦**
www.babysfirsttest.org

**በሚኒሶታ ውስጥ አዲስ ለተወለዱ ህጻናት ስለሚደረግ ምርመራ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እዚህ ጋር ስካን ያድርጉ ወይም ድረ ገጻችንን ይጎብኙ፥**
www.health.state.mn.us/people/newbornscreening

DEPARTMENT OF HEALTH

Minnesota Newborn Screening Program (የሚኔሶታ አዲስ የተወለዱ ህጻናት ምርመራ ፕሮግራም)
www.health.state.mn.us/newbornscreening
P.O. Box 64899, St. Paul, MN 55164
ይህንን መረጃ በሌላ መልኩ ለማግኘት፥
health.newbornscreening@state.mn.usን ያነጋግሩ
ወይም ወደ (800) 664-7772 ይደውሉ *አስተርጓሚዎች አሉ

የተሻሻለበት ቀን 2/2025